የትንቢት ቃል የወንጌል
አገልግሎት

## በሥራ ላይ ያሱ የወደፊት ዕቅዶች

**በጽሁፍ፡-**

- "ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ መንገድ" የተሰኘውን መጽሐፍ በተሻሻለ አማርኛ ተርጉሞ ማቅረብ፣
- "ማራናታ" የተሰኘውን የኤለን ጂ. ኋይት የእለት ተእለት የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መምሪያ ተርጉሞ ማቅረብ፣
- "የተስፋ ያለህ!" የተሰኘ አዲስ የወንድም መልአክ አለማየሁ መጽሐፍ ማቅረብ፣
- "እግዚአብሔር ቃል ገብቷል" የተሰኘውን መጽሐፍ በኦሮሚፋ ቋንቋ ተርጉሞ ማቅረብ።




**በድምጽና በምስል፡-**

"የዘመናት ምኞት" የተሰኘውን መጽሐፍ በትረካ መልክ በድምጽ አንብቦ በመጨረስ ለአድማጮች ማቅረብ፣ የተለያዩ የዝማሬ ካሴቶችና ሲዲዎች እንዲወጡ መደገፍ፣ የስብከት ቪሲዲዎችን በብዛት መስራት፣ የተለያዩ ጠቃሚ ፊልሞችን ወደ አማርኛ ተርጉሞ ማቅረብ።

**በድህረ ገጽ እና በዜና መጽሔት፡-**

ድህረ ገጹን በየጊዜው በአዳዲስ መልቲሚዲያ መረጃዎች በመሙላት ወቅታዊና ጠቃሚ መረጃዎችን የያዙ ዜናዎችን በመጻፍ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ።

**ወንጌል ባለተዳረሰባቸው የአገራችን ክፍሎች የምስራቹን ቃል የሚያሰራጩ ወንጌላዊያንን መደገፍ**

# የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎትን በጸሎትዎ፣ በሃሳብዎ እንዲሁም በገንዘብዎ ይደግፉት።

**የ ት ን ቢ ት ቃ ል**


Yetnbit Kal Ministries
P.O. Box 190346
Addis Ababa
Ethiopia
Tel. +251 911 714976
Email: yetnbitkal@yahoo.com
Web: www.yetnbitkal.org

Yetnbit Kal Ministries
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany




የትንቢት ቃል
የወንጌል አገልግሎት

# የትንቢት ቃል
# የወንጌል አገልግሎት

ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ።
2 ጴጥ. 1፡19



የ ት ን ቢ ት ቃ ል

## የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት

“የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት” በጀርመን አገር በሚገኙ አድቬንቲስት ወንድሞች ተመሥርቶ የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን መስጠት ከጀመረ 11 ዓመታት አሳልፏል። “የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት” የኢትዮጵያ አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን እንድታሰራጭ ከጌታ የተሰጣትን ተልዕኮ እንድትወጣ የሚደግፍ በፈቃደኛ አገልጋዮች የተቋቋመ አገልግሎት ሲሆን ራዕዩ፡- የእግዚአብሔር ቅሬታ ሕዝብ በእውነተኛ የደቀመዝሙርነት ጎዳና እየተጓዘ የኢየሱስ ዳግም ምጻትን ሲያፋጥን ማየት፣ ተልእኮው ደግሞ በጽሑፍ፣ በድምጽ፣ በፊልም፣ በድህረገጽና በዜና መጽሔት ለክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ምጻት የሚያዘጋጁ መንፈሳዊ መልእክቶችን በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጪ ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ወገኖች ማስተላለፍ ነው።




## የጽሑፍ አገልግሎት

**“የትንቢት ቃል”** በሚል ርእስ ለረጅም ጊዜ ስትዘጋጅ የነበረችው አነስተኛ መጽሔት፣ አሁን የመደበኛ መጽሔትን ቅርጽና ይዘት በመያዝ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ መታተም ከጀመረች ከዓመት በላይ እድሜን አስቆጥራለች።

መጽሔቷ የተለያዩ ወቅታዊ ርእሶችን ከማቅረቧም ባሻገር የጽሑፎቹ በጠንካራ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ መደገፍ፣ የአንባቢዎችን ገንቢና የሚያደፋፍር አስተያየት ለአዘጋጆቹ ጆሮ እንዲደርስ አድርጓል።

በመጽሐፍ ደረጃ በ”የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት” ተደርሰውና ተተርጉመው ከተዘጋጁት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

- ❍ “የጸሎት ያለህ!” በወንድም መልአክ አለማየሁ
- ❍ “እግዚአብሔር ቃል ገብቷል” በኤለን ጂ. ኋይት
- ❍ የአዋቂዎች ሰንበት ትምህርት ትርጉም

## የድምጽ እና የፊልም አገልግሎት

እንደሚታወቀው በዘመናችን የንባብ ባህል እየተዳከመ ብዙዎች በሚደመጥና በሚታይ ነገር ላይ ትኩረታቸው የሚሳብበት ሁኔታ በጉልህ ይታያል። በመሆኑም “የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት” ይህንን ዝንባሌ ከግምት ውስጥ በመጨመር የሚከተሉትን የድምጽና የፊልም ስራዎችን በአማርኛ አቅርቧል፡-

**በድምጽ፡-**

- ❍ “የዘመናት ምኞት” ከተሰኘው የኤለን ጂ. ኋይት መጽሐፍ “የህማማት ሳምንት” ትረካ፣
- ❍ የእህት ጁሊያታ ሽብሩ “እስራኤል ሆይ” የሚል የመዝሙር አልበም፣
- ❍ የወንድም ሰላሙ ታገሠ “የክርስቲያን ተስፋ” የሚል የመዝሙር አልበም፣
- ❍ እንዲሁም በአድቬንቲስት አለማቀፍ ሬዲዮ የሚቀርቡ የአማርኛ ፕሮግራሞችን በሲዲ።

**በፊልም፡-**

- ❍ የተለያዩ የስብከት ቪሲዲዎች፡- በፓስተር ጥሩነህ ወልደ ሥላሴ፣ በወንድም መልአክ አለማየሁ፣ በፓስተር በቀለ ገብሬ፣ በወንድም ሮቤል ገዛኸኝ፣ በዶ/ር መርእድ ገብሩ፣ በወንድም ማንደፍሮ አለማየሁ ፣ በፓ/ር በቀለ ብሪ፣እንዲሁም በሌሎች።

- ❍ “የመጨረሻው ፍልሚያ” (ዘ ፋይናል ባትል) የተሰኘው በአድቬንቲስት ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሆሊውድን የፊልም ደረጃ ጠብቆ የተሰራ፣ በክርስቶስ ምጻት ላይ ያነጣጠረ ፊልም ለዛ ባለው ሁኔታ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለእይታ በቅቷል።




- ❍ “ፋና ወጊዎች” (ኪፐርስ ኦፍ ዘ ፍሌም) የተሰኘው ይህ የቤተክርስቲያንን ታሪክ የሚዳስስ ስምንት ክፍሎች ያሉት ጥናታዊ ፊልም ሲሆን፣ አድቬንቲስቶች የታሪክ ግንዳቸውን ያውቁ ዘንድ በአማርኛ ተተርጉሞ ቀርቦአል።

## የድህረ ገጽ እና የኢ-ሜይል አገልግሎት

“የትንቢት ቃል የወንጌል አገልገሎት” የራሱ ድህረ ገጽ ያለው ሲሆን (www.yetnbitkal.org) በዚህም የተለያዩ ጽሑፎችን፣ ስብከቶችን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎችና መልሶችን እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ መንፈሳዊ ማቴሪያሎችን ያቀርባል።

በተጨማሪም በአገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጪ በአድቬንቲስት ቤ/ክ ውስጥ የሚከናወኑትን መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች እየዘገበ ከ 300 በላይ ለሚደርሱ ደምበኞቹ በኢሜይል አድራሻዎቻቸው በየወቅቱ ያሰራጫል።